በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ! አሜን።

***ወንድሞች ሆይ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው ኃጢያተኛውን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢያትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ። የያዕቆብ መ.5፤19-10።***

እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ለሕዝቡ በባሪያዎቹ እየተናገረ፤ ሕዝቡን ከመከራ እና ከመተላለፋቸው እየመለሰ፤ ወደ ክብሩ መንግስት እያፈለሰ፤ ዓለም ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ አሁን እኛ እስከደረስንበት ጊዜ ድረስ ወንጌል ወደ እኛ ደርሷል። ወደፊትም ዓለምን ከመኖር ወደ አለመኖር እስከሚያመጣት ድረት ይኸ ሁኔታ ይቀጥላል። ስለሆነም ሕዝቡ ባለማወቅ ጨለማ ውስጥ ሲተራመስ ፤ ሕዝቡን በጨለማ ውስጥ የማይተው አምላክ በወደደው ጊዜና ስዓት ነገሮችን ከተሰወሩበት ግርዶሽ ውስጥ ወዶ ይገልጣል። ዛሬም ቃሉንም ሆነ ህጉን ካለማወቃችን የተነሳ እንዳንጠፊ የተሰወረውን ገለጠ። ክብር ለስሙ ይሁን።
***ዶግማ ፦ ምንድን ነው?***
***ቀኖና፦ ምንድን ነው?***
***ፍትሐ ነገሥት እና ቃለ አዋድስ?***
እነዚህን የሐይማኖታችንን መሰረቶች እና በውስጣቸው ያለውን የመተዳደሪያ ስርዓት የያዘ ጥልቅ ሚስጥር ፤ ሕዝቡ በሚገባው እና በሚገባዉ መንገድ እንዲረዳ እና እንዲያውቅ ተደረገ። ተማረ፤ ተረዳ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!።

# የዓሣ ግማቱ ከአናቱ!!

መቸም አባባሎች እንበላቸው እንጂ ፤ አባባሎችን ዝም ብለው አበው ትተውልን አልሄዱም።
ታዲያ ቀኖናችን ማለትም ፤ ዋናው ሕገ-መተዳደሪያ፤ የት ነው የተጣሰው?
የመቶ አመት ታሪክ ባላወራም፤ በዚህ በሀያ ዓመት ብቻ የተሰራው ስህተት ለትውልዱ ከበቂ በላይ ነው።

1ኛ. ጳጳስ በሕይወት እያለ እሱን ከመንበሩ ላይ አባሮ ሌላ ጳጳስ መሾም የማይቻል ከሆነ፤ ነገር ግን ጳጳስ ተሽሮ ጳጳስ ሲሾም እንዴት ሲኖዶሱ ይህ መሰረት ያለው የመተዳደሪያ ሕግ ሲጣስ በዝምታ ተቀበለ?
2ኛ. የተሾሙትስ ጳጳስ በፈጣሪ ፈቃድ ወደማያልፈው ዓለም ከሄዱ በኋላ፤ አሁን በሕይወት ያሉትን አራተኛ የነበሩትን አባት ለሐይማኖቱ አንድነት እና ለሕዝቡ ሰላም ለቃለ አዋዲውም መከበር ሲባል ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ሲጠየቅ፤ የለም አምስት ብሎ አራት አይባልም። አምስት ብሎ ስድስት ነው ። በማለት በስምምነት ሲኖዶሱ ስድስተኛ ጳጳስ እንደገና ሲሾምልን፤ የመጀመሪያው ጥፋት ሳያንስ ሁለተኛውንስ ምን ብለን እንለፈው? ለመሆኑ በቀመሩስ ከተሄደ አንድ ሰው ሲሞት የሕዝብ ቁጥር ይቀንሳል እንጂ ይጨምራል እንደ? በእርግጥ ሰዎች ሲሞቱ ፤ ሰዎች ይወለዳሉ። ግን ጳጳስ ሆኖ የተወለደ አልሰማንም። ከሲኖዶሱ ውስጥ አንድ ጳጳስ ከሞተ ቁጥሩ ዝቅ የሚለው ወደ አራት እንጂ እንደት ወደ ስድስት ይዘላል?
የእኔ ትልቁ ጥያቄ ግን ሲኖዶሱ እራሱ ቃለ አዋዲውን የጣሰ ወይም በቃለ አዋዲው የማይመራ የመሆኑ ላይ ነው።

በስነ-ምግባር ብልሹነት የሚታሙት፤ በሥልጣን ጥማት የሚተቹት፤ እራሳችንን ለክርስቶስ ፍቅር ስንል ሰልበናል ዓለምን ንቀናል እያሉ፤ ነገር ግን በቀሚሳቸው ውስጥ በታጠቁት ሱሪ ወንድ መሆናቸውን እያስመሰከሩ የሚገኙትን መንፈሳዊ አባቶች ተብዬዎች፤ በሥጋም አባቶች እንደሆኑ እየተወራላቸው ስንሰማ ከማሳፈር አልፎ ይዘገንናል።
በድንግልናቸው ካፈሩ በሥጋዊ ምኞት ከሚቃጠሉ ቆባቸውን በክብር አስቀምጠው ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለው የአምላካችንን ቤተ መቅደስ ሳያረክሱ እንደ ማንኛውም ሕዝበ ክርስቲያን ሆነው ቢኖሩ አምላክ አይፈርድባቸውም።
ምክንያቱም *በ1ኛ ቆረንቶስ 7፤26-27 ፤ዳሩ ግን ማግባት ወደሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ስለ ድንግልናው ያፈረ ሰው ቢኖር የወደደውን ያድርግ፤ቢያገባም ኃጢያት የለበትም። ሳይናወጥ በልቡ የፀና ግን ግድ የለበትም፤ የወደደውን እንዲያደርግ ተፈቅዶለታል፤ ድንግልናውንም በልቡ ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና መልካም አደረገ።*

ስለዚህ ለማግባት የጊዜ ገደብ ስለሌለው ልቡ አልሞት ያለው መነኩሴ በስልሳ አመቱም ቢሆን አግብቶ ይገላገል እንጂ የእግዚአብሔርን ቤት ለምን ያረክሳል?
እግዚአብሔር ክብሩ በሚያረክሰው ሰነፍ ባሪያ ላይ ቁጣው ይነዳል።ትግስቱ ለንስሐ እንድንበቃ እንጂ ተኝቶ እንዳይመስለን። ለዚህ ነው ንገሡ ብልጣሶር የፈጣሪን ክብር በመዳፈር በቤቱ በተቀናጣ ጊዜ፤ ከሚያስፈራው ግርማው የቁጣ ጣት የወጣችው። ብልጣሶር የእግዚአብሔርን ግርማና ክብር ቁጣውንም ትግስቱንም በአባቱ የተደረገውንም ሁሉ የሚያውቅ ሆኖ ሳለ በዘመኑ ግን ጠገበ፤ ፈጣሪን አረሳ። እግዚአብሔር ልባቸው ለሰባ ሳይሆን አምላክነቱ ፤ ልባቸው ቃሉን ለሰማ ብቻ ነው።
ስለዚህም፤ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፦ ***ትንፋሽህንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ አላከበርከውም።ስለዚህም እነዚህ የእጅ ጣቶች ከእርሱ ዘንድ ተልከዋል፤ይህም ጽሕፈት ተጽፎአል። የተጻፈውም ጽሕፈት፦ ማኔ፤ ቴቄል ፋሬስ ማለት ነው።የነገሩም ፍቺ ይህ ነው፤ማኔ ማለት፤እግዚአብሔር መንግሥትህን ቈጠረው፤ፈጸመውም ማለት ነው።ቴቄል ማለት፦በሚዛን ተመዘንህ ፤ቀለህም ተገኘህ ማለት ነው። ፋሬስ ማለት፦መንግሥትህ ተከፈለ ፤ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎችም ተሰጠ ማለት ነው።ት.ዳንኤ.5፤23-28 ።***
ከዚህ ቃል ብዙ ተምረው አስተማሪዎች መሆን ሲገባቸው ጭራሽ በዓለም ያሉት እንኳን የሚጸየፉትን ነውር፤ መነኩሴው እና ጳጳሱ ዘማዊ ከሆነ ምዕመኑን ስለ ዝሙት ምን ብለው ሊያስተምሩት ነው?
ታዲያ በገዛ እጃቸው የቀበሩት ወንጌል እያሳደዳቸው ሀጢያትን እንደ ውሃ ጠጥተው  ልባቸው ያልተገራና ያለደከመ ጎረምሶች በየዋሁ ሕዝበ ክርስቲያን ላይ የተፈናጠጡ ዲያጎኖች ማን ሊገላግለን ነው?  ብዬ እራሴን ስጠይቅ፤ መልሱ በጣም ግልጽ ነው። ሕዝበ ክርስቲያኑ እራሱን ከፈጣሪው እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሚገባ ማገናኘት መቻል አለበት። ያን ጊዜ አምልኮ እና ስግደት ለማን እንደሚገባ፤ አክብሮት ደግሞ ለማን እንደሚሰጥ ያውቃል። ዓይኑን ከሰው ላይ ያነሳል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ***በት.ዘካርያስ 1፤3-6 ላይ እንዲህ ይላል፦ ስለዚህ እንዲህ በላቸው፦የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ወደ እኔ ተመለሱ ፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፤እኔም ወደ***

***እናንተ እመለሳለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።***
***<u>የቀደሙት ነቢያት ለአባቶቻችሁ እንዲህ ብለው ሰብከዋል፦የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ ፤ እነርሱ ግን አልሰሙም፤እኔንም አላደመጡም እንደ እነርሱ አትሁኑ፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።</u>***

## ወደ እኔ ተመለሱ!

በዚህ የእግዚአብሔር ጊዜ ሊገለጥ ጥንስሱ በተጀመረበት ዘመን ሰይጣን ዓለምን እያራወጠበት፤ ፍጥረትን እያስጨነቀ ባለበት ዘመን ፤ እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው ነገር ቢኖር፤ ከቃሉ እንደምንረዳው ሕዝቡ በእውነት እና በፍጹም ልብ ወደ እሱ እንድንመለስ ነው። እርሱም ፊቱን እንደሚመልስ እና እንደሚራራልን ይናገራል።
ይህን ሕዝብ ፊቱን ወደ ፈጣሪው እንዲመልስ እረኞቹ መች አገዱት። እግዚአብሔር ወደሚፈልግበት መስክ መቸ አሰማሩት። ለራሳቸው የተሰማሩበት ቦታ መች አማረና!። ከሕዝቡ ይልቅ ካህናቱ ቦታቸውን ስተው ጠፉ።

በቤቱ ዘመናትን የቆጠሩ ካህናት አባቶች ነን ባዮች፤ በፊቱ በንስሀ፤ በእርቅና በይቅርታ መውደቅ ካልጀመሩ፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ እንደት ዓይነት መነቃቃት ሊኖርው ይችላል? በተለያየ የግል ፍላጎት እና ጥቅም እራሳቸውን ያጠላለፉ ጳጳሳትና ካህናት፤ ከራሳቸው ላይ አሽቀንጥረው የጣሉትን የፈጣሪን ፀጋ ከእነሱ እንደራቀ እንኳን የማያስተውሉ፤ በትዕቢት የተወጠረ ልብ የተሸከሙ፤ እራሳቸውን ከፈጣሪ እኩል አወዳድረው በማናለብኝነት ለሕዝቡ የማይመቹ ሆነው ስለተቀመጡ፤ እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ መልካም ነገር ለማድረግ ተቸገረ።

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምናየው፤ ምህረት እንዲመጣ አለቆች ዝቅ ብለው ፈጣሪያቸውን መማፀን አለባቸው። ***ት.ኢሳ 40፤3-5 የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፤ ለአምላካችንም ጎዳና በበረሀ አስተካክሉ።ሸለቆው ሁሉ ከፍ***

***ይላል፣ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፣ ጠማማውም ይቃናል፣ ሰርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል፣ የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፣ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፣ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና።***

ከቃሉ እንደምናየው፦ምህረት እንዲመጣ፣ የስደትና የመከራ ገፈት ቀማሽ መሆናችን እንዲያበቃ ካስፈለገ ፣ ከሰው እስከ እንሰሳ ከአርባ ዓመት በላይ በርሃብና በቸነፈር መድቀቃችን እንዲያበቃ ካስፈለገ፣ የልመና ጥሬ ለወገኖቻችን እንደ ዝናብ ጠብታ መናፈቃቸው እንዲያበቃ ካስፈለገ፣ ከዓለም መንግሥታት ይልቅ በአምላካችን እጅ ምድራችን እንድትዳሰስ ካስፈለገ፣ የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ደስ እንዲያሰኘን ካስፈለገ፣ ቤቱ የፀሎት ቤት እንዲሆንልን ካስፈለገ፣ በከበረው መንበሩ ላይ ቤቱን እያረከሱና እየዘበቱበት ያሉ ሁሉ በፊቱ በንስሀና በእንባ እንደ ልበ አምላክ ዳዊት በራሳቸው ላይ ትቢያ ነስንሰው በፊቱ መውደቅ አለባቸው።

እነሱ ለህዝቡ ያላስተማሩትን ይቅርታ እና ንስሀ መግባት እንደት ከህዝቡ ይፈልጋሉ?

ይህ ካልሆነ ግን በጭንቅላታቸው ላይ ቆልለው የተሸከሙት እና ሕዝብን የሚያስፈራሩበት ጨርቅ፣ የሸክም ብዛት እና እዳ እንዳይሆንባቸው ያስፈራል ብዬ አስባለሁ።

***ለኃጢያተኛ ሞገስ ቢደረግለት፣ ጽድቅን አይማርም።በቅኖች ምድር ክፉን ነገር ያደርጋል።የእግዚአብሔርንም ግርማ አያይም።ት.ኢሳ 26፣10***

ከአባቶች ተብየዎች ሥራ እና አሳፋሪ ተግባር የተነሳ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑ ወደ ቤተክርስቲያን እንሂድ ለሚለው ነገር እግሩ እየተሰነካከለ የመጣበት ጊዜ ነው።

ከደስታው ይልቅ ቁዘማው እና ማመንታቱ በዛ። የእግዚአብሔርም ቃል እራሱ በውስጣችን ማረፊያ ቦታ እንዳያገኝ እንቅፋት ሆኑብን።

በቃሉ እና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አድገንና ጎልብተን ሌሎችን ማዳን ሲኖርብን፣  እንኳን ከውጭ ያሉትን ልናድን ቀርቶ ከቤት ያሉትን ካልወጣችሁ እያሉ ለተራበ አውሬ እየሰጡ የእግዚአብሔርን ቤት ባዶ አደረጉት።

እየተገፉ የጠፉውም ሕዝብ በምላሳቸው ጎራደ መናፍቅ እየተባለ ይሰደባል።
እየተፍገመገመ  በቤቱ የሚንገዳገደውንም ሕዝብ እንዳይወድቅ እግዚአብሔር በባሪያው ሊታደገው ሲነሳ የክርስቶስ ስም ሲጠራ በቤተ መቅደስ ውስጥ ያወራጫቸዋል። ሕዝቡን በሚነዙት አዚም እንዳይንቀሳቀስ ተጎታች ጋሪ እንዲሆን አድርገውታል።
እግዚአብሔር ፦ ስሙን የሚጠራውን ሕዝብ ከቦታ ወደ ቦታ ሲያንቀሳቅስ ዓላማ አለው።
ለዓላማው መሳካት ግን ታዛዥ ባሪያዎች ይፈልጋል። እንደ እነ ኢሳያስ ‘ ***እነሆኝ ፤እኔን ላከኝ’*** የሚሉ።
ልቤ ብዙ ነገር እያሰበ በባቡር ስጓዝ ዓይኔ አንድ መጽሔት ላይ ተወርውሮ አረፈ።
አንስቶ ሳገላብጠው፤ ዓይኔን ብቻ ሳይሆን ልቤንና ዓይምሮዬን የሚስብ ነገር አየሁ። እየተንገዳገድኩ ባነበብኩት ጽሑፍ፤ ልቤ ከውስጥ ክፉኛ መታ፤ ዓይኖቹ በእንባ ተሞሉ። ቃሉን በትልቁ አጉልተው ጽፈውታል። እንዲህ ይላል፦ *’WE WANTED TO SHOW THAT PORNOGRAPHY IS GOOD FUN BUT DOESN’T  LEAD TO EVERLASTING HAPPINESS’*

አዎ! በዚች እኛው በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሰዎች በሰይጣን እግር ብረት ታስረው ይማቅቃሉ። መውጫ ቀዳዳ ጠፍቶባቸው ሰቆቃቸውንም ሆነ ነውራቸውን ያዳማጭ ያለህ እያሉ፤ በየሜዳው ያንጠባጥባሉ። በብርና በወርቅ ቢዘፈቁም ሰላም እና እረፍት በማጣት ሕይወት ይማቅቃሉ። ያዳኝ ያለህ ይላሉ።
በመንፈስ ጭንቀት በሽታ ተወጥረው ከዚያ ለመላቀቅ በተለያየ ሱስ ተይዘው ፉዞ የሆኑ ባለጠጎችን ቤት ይቁጠራቸው። ይህን ሁሉ የሰላም ርሀብተኛ ሠላም እንዲቀምስ የማድረጉ ሥራ ግን የማን ይመስለን ይሆን? ሰላም እና እረፍት ራባቸው እንጂ፤ ገንዘባቸውን እና ስንዴውንማ እየወሰዱ ለተራበው ሕዝብ ይዘረግፉለታል።
ታዲያ እግዚአብሔር እኛን በወንጌል ሲያጠግብ፤ እነሱ ስንዴውን ለኛ እየወሰዱ እንደሚዘረግፉት፤ እኛ ያውም በገዛ ሀገራቸው ቁጭ ብለን፤ ጌታ በክብር አስቀምጠን ወንጌልን መዝራት ሲገባን ጭራሽ በቤተክርስቲያናችን የፀብ ዘሪዎች በመሆን ታወቅን!።

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው፤ ነብያቶችም ሆኑ ሐዋርያቶች ከጃፓን፤ ከቻይና፤ ከራሽያ ፤ ከእንግሊዝ፤ ከአሜሪካም ሆነ ከሌሎቹ  አህጉራት እንዳልተነሱ ግልጽ ነው።
ስለዚህ ለዚህ ወንጌል ላልደረሰው ሕዝብ ፤ ወንጌልን የማድረስ ሀላፊነቱ የማን ይመስለናል? አትጠራጠሩ ሥራው የኛ ነበር።
*ት.ሕዝቅ 3፤4-7 እንዲህም አለኝ፦ የሰው ልጅ ሆይ ተነስተህ ወደ እስራኤል ቤት ሂድ ፤ቃሌንም ንገራቸው።ወደ እስራኤል ቤት እንጂ ንግግራቸው ወደ ጠለቀው ቋንቋቸውም ወደማይታወቅ ሕዝብ አልተላክህምና።ንግግራቸው ወደማይታወቅ ቃላቸውንም ታውቅ ዘንድ ወደማይቻልህ ሕዝብ አልላኩህም።ወደ እነዚያ ልኬህ ቢሆን ኖሮ በሰሙህ ነበር።ነገር ግን የእስራኤል ቤት ሁሉ የጠነከረ ግንባርና የደነደነ ልብ አላቸውና እኔንም መስማት እንቢ ብለዋል እና የእስራኤል ቤት አንተን አይሰሙም።*

ይኸ ቋንቋው ያልታወቀ የተባለ ሕዝብ ለወንጌል ልቡ ምን ያህል የተከፈተ እንደሆነ እግዚአብሔር አምላክ ተናግሯል።
እኛ ግን ወንጌልን በማድረስ ለማንታዘዘው ወዮልን!!
የቀመስነውን ፍቅር ለሌሎች ለማናቀምሰው፤ ያገኘነውን ሰላም ሌሎችም አግኝተው እንዳያርፉ ከክርስቶስ ክብር ተካፋዮች እንዳይሆኑ በሩን ለምንዘጋ ፤ አንደበታችን ለምስክርነት ላልተከፈተ ወዮልን!
የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ማህፀን ላይ በመንፈስ ቅዱስ የመፀለሉ ሚስጥር፤
ሥጋን ለብሶ የተወለደበት መለኮትን ሥጋ ያደረገው፤ ሰማይና ምድርን የፈጠረ፤
ሰውን ከምድር አፈር ያበጀውን ጌታ፤ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር እንዲመጣ ያደረገው ዋናውን እና ትልቁን እውነት ስንመለከት፤ የሰውን ልጅ ከዘላለም ሞት ፍርድ፤ ከገሀነም እሳት ለማስመለጥ ነው።
እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከሰማይ ሆኖ ሲመለከት፤ላላዘጋጀለት እና ላልተመኘለት ነገር በመከራና በኃጢያት ውስጥ ሲዳክር እያየ ዝም ማለት አልቻለም።
ስለዚህ የሰው ልጅ ከመከራ ያመልጥ ዘንድ እግዚአብሔር ሰው ሆነ!!።

የሰውን ሞት ሞተ። የማይሞተው አምላክ ሞትን ቀምሶ በእርሱ ሞት ለእኛ የዘላለም ሕይወትን ሰጠን። ከሞት አስመለጠን። *በ2ኛመ.ነገሥት 19፤30-31 ላይ፤ ያመለጠው የይሁዳ ቤት ቅሬታ ሥሩን ወደ ታች ይሰድዳል፤ ወደ ላይም ያፈራል።ከኢየሩሳሌም ቅሬታ ከጽዮንም ተራራ ያመለጡት የወጣሉና ፤ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።*

## እግዚአብሔር ያስመልጣል!

አዎ! እግዚአብሔር ሕዝቡን ከመከራ ከጭንቅ ያስመልጣል። የሕዝቡ ሥቃይና መከራ ሲበዛ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከጠላት ሊታደግ በቅንዓት ይነሳል።
ብዙዎቻችንን ከስንት መከራ አስመልጦ በቤቱ ሰብስቦናል። ማምለጣችን በጉልበት፤ በዘዴ ወይም በገንዘብ እና በእውቀታችን አይደለም።
ነገር ግን አምላካችን በከበረው ክንዱ ከጠላት ወጥመድ አስመለጠን። ያመለጠ ሁሉ የማምለጡ ውጤት ሌሎችንም ለማስመለጥ ነው።
የእውነት አምልጠን ከሆነ አንድ ነገር ይጠበቅብናል።
ይኸውም ወደ ውስጥ ስር መስደድ፤ ወደ ላይ ደግሞ በፍቅርና በትህትና ማደግ ነው። የሚታይ ፍሬ ማፍራት አለብን።
ይህ ለክርስቲያናዊ ሕይወት አማራጭ ሳይሆን ግዴታ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን በጧት በማታ ሲመግበን እንድናድግ እንጂ ቀጭጨን እንድንኖር አይደለም።
ሰው የወለደውን ልጅ ተንከባክቦ አሳድጎ ለከበረ ነገር ሲበቃ ማየት እንጂ የሚይስደስተው፤ ልጁ ተሽመድምዶ ቢቀርበት፤ መቆም እና መራመድ ባለበት እድሜ እየዳኸ ዘመኑ ዘመነ ዳዴ ቢሆንበት ፤ልጅነቱን ባይጠላውም ልቡ የማይሰበርበት ወላጅ ማን አለ?
እግዚአብሔርማ ከዚህ ይልቅ በደሙ የገዛን በስቃይ አምጦ በሞቱ የወለደን ፤ ፍሬ አልባ ስንሆንበት እንደት ያዝን!!
እኛን በዚች ምድር የማምጣት ትርጉሙ ሌላ ምንም ዓላማ የለውም። የጠፉትን ሕዝቡን እንዲያድን እንጂ።

በእንግሊዝ ሀገር ላይ አስቀምጦ የምናመልክበት ሕንጻ ማዘጋጀቱ፡ የጠፉትን በጎቹን እንድንሰበስብለት እንጂ፤ ንፍሮ እያነፈርን እንድንቅምበት አይደለም።
ወይም እንድንራኮትበትም አይደለም።
ታዲያ በየቦታው ይህ ሕዝብ ነውሩን እየዘረገፈ የሰው ያለህ ሲል፡ ግብረ-ሰዶማዊያን  ዓለምን ሲያጥለቀልቋት፤ ክርስቶስ ኢየሱስ ነፃ ያወጣሀል ወንድሜ ሆይ ና! ወደ ቤቱ፤ ከእርሱ ዘንድ እረፍት እና ሰላም አለ ብለን መመስከር የሚገባን ሰዓት፤ አይደለም ብለን እናስባለን?
ሳምራዊቷ በዚያ በጠራራ ፀሐይ እራሷን ከሰው ሁሉ ሰውራ፤ ያጎበጣትን እና የሚያስጨንቃትን በልቧ እንዳሸንክታብ ያጠለቀችውን ወደ ታች እየጎተተ ከሰው በታች ያደረጋትን ኃጢያት እያሰላሰለች በምድረበዳ ውሃ ፍለጋ ስትባዝን፤ በጥም ለተንገበገበው የውስጥ መቃተቷ፤ ለውስጧ ጎደሎ፤ ለውስጧ ችግር መፍትሄ፤  ለነፍሷ ሰላም፤  ለሥጋዋም እረፍት የሚሰጣትን ንጉስ የናዝሬቱን ኢየሱስን ስታገኝ፤ ይኸንን መልካም ዜና ለራሷ ብቻ ዋጥ አድርጋ ተመልሳ እንስራዋን ተሸክማ ወደ ቤቷ አልሄደችም ከዚህ ይልቅ ይህን መልካም ዜና ልትመሰክር ላልሰሙት ልታሰማ ወደ ከተማ ሮጠች። ***ዮሐ 4፤ 28-30 ሴቲቱም፦እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች፤ለሰዎችም፦ያደረግሁትን የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች።ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።***
እውነት አድርጋለች። ከዚህ የበለጠ ሊወራ እና ሊታወጅ የሚገባ ምን መልካም ነገር አለ።
በምንም ይገመት ንብረቷ የሆነውን፤ እንስራዋን ከነማንገቻው ከነ ጣሳው ጥላ ውልቅ አለች።
ለዚያች ምስኪን ሳምራዊት በዘመኑ የእንስራው ዋጋ ከአቅሟ በላይ ይሆን ይሆናል። ግን ለክርስቶስ ሲባል ምን የማይጣል ነገር አለ። ክብር፤ ዝና፤ ወይስ እውቀት? ሁሉም በፊቱ አመድ የሚሆኑ የጊዜው ትርኪ ምርኪ እንደሆኑ ይቺ ሳምራዊት ገብቷት፤ ከሸክም ለሚያሳርፈው ጌታ የርሷን ኮተት በእርሱ ላይ ትታ ወንጌልን ልትዘራ ሮጠች።
ለዚህ ነው ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***በማቴ.11፤28-30 ላይ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ***

***ተሸከሙ፤ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ፦ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ።ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።*** **ብሎ ያለው።**

**ታዲያ ዛሬ በምንኖርበት ምድር እነዚህ ሰላም የናፈቃቸው፤ ሰላም እንደ ውሃ የጠማቸው፤ በተከበረውና በተቀደሰው የክርስቶስ ቤተ መቅደስ ላይ/በሥጋቸው ላይ /ነውርን እንደ ጽድቅ ተሸክመው፤ የአመጻንና የበደልን ምንነት ዘንግተው በዓለም ፊት ሥጋቸውን በማቆሸሽ እና ላልባሌ ነገር በማስገዛት ሰላም እናገኝ ይሆናል ብለው ኃጢያትን እንደ ውሃ ሲጠጡ፤ ሲሴስኑ ፤ ስይጣን አስሮ ሲጫወትባቸው፤ ሰውነታቸውን እንደ እንጀራ እየበላ ለአደባባይ መሳቂያ ሲያደርጋቸው፤ ግን ውስጣቸው ሰላም እንደሌላቸው መልሰው ባደባባይ ሲያለቅሱ መስማት እንደት የሚገርም ትንግርት ነው። ታዲያ ክርስትና ለእኛ ብቻ መች ሆነ። ክርስቶስ የሞተው ለዓለም ሁሉ ነው።**

**ከሱቅ ገብተን አምሮን የገዛነውን ልብስ እንጅ እኛ ብቻ የምንለብሰው፤ ክርስቶስንማ ለዓለም ሁሉ የማሰማት ግደታ አለብን።**

**የለንደን ደብረጽዮን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህ ሁሉ ኃላፊነት እያለባት፤ እራሷን ከህብረተሰቡ ጋር አገናኝታ ስንት ነፍስ የማዳን ሥራ መስራት ሲገባት፤ የጋን መብራት ካልሆንኩ ብላ፤ ለሌላው ዓለም ትተርፋለች የተባለችው፤ እንኳንስ ለዓለም የወንጌል ምስክር ልትሆን ቀርቶ፤ በርሃብ በዓለም በአንደኛ ደረጃ እንደምትታወቀው ሁሉ ፤ አሁን ደግሞ በዚህ በክፉ ክርሥቲያናዊ ሥራ ምዕመኖቿን በመከፋፈልና በማበጣበጥ አንደኝነቷን አስመሰከረች!!**

**ታዲያ የእውነት ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር የዘረጋችው ለምን ይሆን ? ለንስሐ ? ወይስ ለበረከት?**

**እኔና የእኔን ሀሳብ ለሚደፉ ሁሉ ፍርዱን ቅን ልቦና ላላቸው እንተዋለን።**

**በዕብሪት ቤቱን ዘግተንለት አርፈናልና ። እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ!!**

*ከለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን፤*
*አበባ አመደ*
*ወስብሐት ለእግዚአብሔር!*